አቢሲንያ ባንክ
Bank of Abyssinia

# የሴቶች የስራ ፈጠራ፣ የሙዚቃና የግጥም ውድድር !

## በውድድሩ ለመሳተፍና ሥጦታዎቹን ለማግኘት የተቀመጡ መሥፈርቶች እና የውድድሩ ሂደት

1. አስቀድሞ የአቢሲንያ ባንክ የፌስቡክ ገፅን https://www.facebook.com/BoAeth ይቀላቀሉ፡፡

2. በሁለቱም ዘርፍ ማለትም ለሙዚቃና ለግጥም ውድድሩ በሙያው በቂ ልምድ ያላቸው ሶስት ሶስት ዳኞች የተመረጡ ሲሆን፣ ለወድድር የሚላኩትን የሙዚቃና የግጥም ሥራዎች በመገምገም ከእያንዳንዱ ዘርፍ አስር አስር ሥራዎችን በሚያስቀምጧቸው መሥፈርቶች አወዳድረው ይመርጣሉ፡፡ በመቀጠልም ከእያንዳንዱ ዘርፍ የተመረጡት አስር አስር የጥበብ ሥራዎች በድጋሚ ተመልካቾች ድምፅ እንዲሰጡበት በባንካችን የፌስቡክ ገፅ ላይ የሚለጠፍ ይሆናል፡፡ በመጨረሻም የባንካችን አስመራጭ ኮሚቴ አባላት በተገኙበት የተመልካቾች ድምፅ ተቆጥሮ ከአስሮቹ ሶስት ሶስት የመጨረሻ አሸናፊዎች የሚለዩ ይሆናል፡፡

3. የሥራ ፈጣሪ ሴቶች በአነስተኛ የወለድ ምጣኔና ካለመያዣ እስከ ብር 300,000.00 (ሦስት መቶ ሺህ) የብድር አገልግሎት ለማግኘት በውድድሩ ለመሳተፍ መሟላት የሚገባቸው መሥፈርቶች

- ✓ በተሰማሩበት የሥራ መስክ የንግድ ወይም የማምረት ፍቃድ፤
- ✓ የታክስ ክፍያ መለያ ቁጥር፤
- ✓ ቢያንስ ለአንድ ዓመት በሥራ መኖራቸውን የሚገልፅ ማስረጃ፤
- ✓ የአንድ ዓመት የባንክ የሂሳብ መግለጫ (Bank Statement)፤
- ✓ በሥራችሁ ያሉትን የሰራተኞች ቁጥር የሚያሳይ ማስረጃ፤
- ✓ የተሰማሩበትን የሥራ መስክ፣ እሳኩን የተገኘውን ውጤት፣ ብድሩ ያስፈለገበትን ምክንያትና ሊከፈልበት የሚችልበትን ጊዜ፣ሥራው ያለው ተግዳሮትና ወደፊት ያለውን ተስፋ ያካተተ ማመልከቻ ማቅረብ ያስፈልጋል፡፡

* ከአንድ በላይ ቅርንጫፍ ወይም ዲስትሪክት ጥያቄ ማቅረብ ከውድድሩ ውጪ የሚደረግ መሆኑን በዚሁ አጋጣሚ መግለፅ እንወዳለን፡፡እነዚህን ቀላል ቅደም ተከተሎች የተከተሉ ተወዳዳሪዎች የሽልማት እጩነት ውስጥ ይካተታሉ፡፡